

# The Return to Work scheme and work injury support ወደ ሥራ የመመለስ እቅድና የሥራ ላይ ጉዳት ድጋፍ

ወደ ሥራ መመለስደአ የደቡብ አውስትራሊያን የንግድ ድርጅቶችን እና ሠራትኞቻቸውን በሥራ ላይ ሊደርስ ለሚችል አደጋ የሚውል መድህን ይሰጣሉ።

ወደ ሥራ መመለስ ቅንብር፣ በጣም ጉዳት የደረሰባቸውን ግለሰቦች ካልደረሰባቸው ይልቅ የተለየ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ይገነዘባል።.

## ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የሚደረገው ድጋፍ የሚከተልውን ሊመስል ይችላል፡

- ሊያገኙት ላልቻሉት ደሞዝ የገቢ ድጎማ ድጋፍ – በአጠቃላይ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሊደርስ ለሚችል ጊዜ፣
- አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ዓመት ሊደርስ ለሚችል ጊዜ፣ ተመጣጣኝና አስፈላጊ ህክምና እና እንክብካቤ መስጠት፣
- አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ዓመት ሊደርስ ለሚችል ጊዜ፣ እንደ ሥራ ምደባና የእንደጋና ስልጠና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን መስጠት፣

## ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የሚደረገው ድጋፍ የሚከተልውን ሊመስል ይችላል፡

- የጡርታ ጊዜአቸው እስኪደርስ የገቢ ድጋፍ፣
- እስከ ህይወታቸው መጨረሻ ድረስ፣ ተመጣጣኝና አስፈላጊ ህክምና እና እንክብካቤ መስጠት፣
- ጥያቄው ከቀረበ፣ ወደ ሥራ የመመለስ አገልግሎት።

በሥራ ላይ አደጋ ከደረሰብዎት ምናልባትም ከሁለት ሳምንት በላይ ከሥራ ሊቀሩ ይችሉ ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የይገባኛል ወኪልዎ የጉዳይ ሥራ አስኪያጁን የሥራ ቦታዎን እንዲጎበኝና ከእርስዎና ከአሠሪዎ ጋር ለመገኛነትና ሕክምና ከሚያደርጉበት ቦታ ጋር ለማናኘት እንዲችል ወደቦታው ለመላክ ጥረት ያደርጋል። ይህም የሚሆነው እንደ አስፈላጊነቱ እንክብካቤና የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማድረግ እንዲሻልዎና በተቻለ ፍጥነት ወደ ሥራዎ እንዲመለሱ ለመርዳት ነው። ይህ የፊት ለፊት የሥራ ቦታ ጉብኝቶች አደጋው መድረሱ እንደታወቀ በተቻለ መጠን በአፋጣኝ ይደረጋል።



www.rtwsa.com
13 18 55
Government of South Australia

## What to do if you are injured
## ጉዳት ከደረሰብዎት ምን ማድረግ እንደሚኖርብዎ

በሥራ ቦታ ገዳት ደርሶብዎ ከሆነ፣ ሊከተሏቸው የሚገቡ በጣም አስፈላጊና በርካታ ደረጃዎች መውሰድ ይኖርብዎታል።

### ደረጃ 1: አስፈላጊውን ሕክምና ይሹ።

### ደረጃ 2: ለአሠሪዎ ያመልክቱ።

ከታቻለ፣ አደጋው በደረሰ በ24 ሰዓት ውስጥ ለአሠሪዎ በጽሑፍ ወይም በቃል መንገር ይኖርብዎታል። እርስዎ ማድረግ ካልቻሉ፣ ተወካይ፣ ማለትም የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ለአሠሪዎ ሊነግርልዎት ይችላል።

### ደረጃ 3: ወደ ዶክተር ይሂዱ

ዶክተሩ ጉዳትዎን በመገምገም ምን አይነት ጉዳት እንደደረሰብዎ፣ ምን አይነት ህክምና እንደሚያስፈልግዎ እንዲሁም ህክምናው በየስንት ጊዜና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚደረግልዎ ይወስናል። ለአሠሪዎ የይገባኛል ወኪል ከሥራ እረፍት ለመውሰድና ይገባኛል የሚጠይቁ ከሆነ የመጠየቂያውን ቅጽ እንዲሰጥዎ የመሥራት አቅምዎን የሚገመግም ሰርቲፊኬት ይሰጥዎታል።

### ደረጃ 4: ይገባኛል ይጠይቁ

ጉዳትዎ ከሥራዎ የሚያስተጓጉልዎ ከሆነ ወይም የህክምናም ሆነ ሌላ ወጪ የሚያስከትልብዎ ከሆነና የጉዳት ካሳ የይገባኛል ጥያቄ ማድረግ ከፈለጉ፣ የይገባኛል ቅጹን መሙላት ይኖርብዎታል።

የሚቻል ከሆነ፣ የይገባኛል ቅጹን ከአሠሪዎ ጋር ሆነው መሙላት ይኖርብዎታል። ይህን በማድረግዎ ለአሠሪዎ ስለሁኔታዎ በማሳወቅ ሊደርግልዎት ስለሚችለው ድጋፍ ለመወያየትና በሥራዎ ላይ እንዲቆዩ ወይም ጉዳትዎ የሚፈቅድልዎ ከሆነ ወደ ሥራዎ በተቻለ ፍጥነት እንዲመለሱ ለማድረግ እድል ይሰጣል። ብተጨማሪም ለይገባኛሉ ጥያቄ ውሳኔ እንዲረዳ፣ ትክክለኛውን እና ሙሉውን መረጃ ለመስጠት ያገለግላል። አሠሪውና ሠራተኛው አንድ ላይ ቅጹን መሙላት ካልቻሉ፤ ቅጹን ለየብቻ መሙላት ይቻላል።

የይገባኛል ቅጹ ይገባኛሉ ለህክምና ወጪ፣ ለማይከፈልዎት ደሞዝ ወይም ለሁለቱም መሆኑን ለማሳየት ያስችልዎታል።

አሠሪዎ የይገባኛል ቅጹን ግልባጭና ህክምናዎን ከሚከታተለው ዶክተር የሚሰጥዎትን የመሥራት አቅምዎን የሚገመግመውን ሰርቲፊኬት ከእርስዎ ከተቀበሉ በኋላ ለይገባኛል ወኪሉ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ማስረከብ ይኖርባቸዋል።

የይገባኛል ወኪሉ ስለ ጉዳትዎ በተቻለ መጠን ቀደም ብሎ ቢያውቅ፣ በተቻለ ፍጥነት አገግመው ወደ ሥራ መመለስ እንዲችሉ፣ ከሚያስፈልግዎ ህክምና፣ እንክብካቤና ድጋፍ ሰጪዎች ጋር እንዲገናኙ ዝግጅት ለማድረግ ያስችላቸዋል። የይገባኛል ጥያቄውን ለማድረግ እርስዎ ወይም አሠሪዎ የአሠሪዎችን የይገባኛል ወኪል መገናኘት ይችላሉ።

**Gallagher Bassett Services Pty Ltd**
**GPO Box 1772, Adelaide SA 5001**
**newclaims@gb.rtwsa.com**
**Fax (08) 8177 8451**
**www.gallagherbassett.com.au**
**Phone (08) 8177 8450 or free call 1800 664 079**

**Employers Mutual SA**
**GPO Box 2575, Adelaide SA 5001**
**newclaims@employersmutualsa.com.au**
**Fax (08) 8127 1200**
**www.employersmutual.com.au**
**Phone (08) 8127 1100 or 1300 365 105**

አብዛኞዎቹ ትልልቆቹ የደቡብ አውስትራሊያ የግልና የሕዝብ ድርጅቶች የየራሳቸውን የካሳ የይገባኛል ጥያቄዎችን ለማስተዳደር የሚያስችል የግል-መድህን አላቸው። የግል-መድህን ላላቸው የንግድ ድርጅቶች ተቀጥረው ከሆነና በሥራ ላይ ጉዳት ከደረሰብዎ፣ የጉዳት ካሳ ይገባኛልን በተመለከተ አሰሪዎን ማነጋገር ይኖርብዎታል።

## Your obligations Sus Obligaciones የእርስዎ ግዴታዎች

በመልካም ሁኔታ አገግመውና ወደ ሥራ የሚመለሱበትን ውጤት ለማግኘት፣ የሚከተሉትን ከእርስዎ እንጠብቃለን፡

- በሥራ ላይ ስለደረሰብዎት ጉዳት አሰሠሪዎን ባተቻለ ፍጥነት ማነጋገር (ከተቻለ በ24 ሰዓት ውስጥ)፣
- ይገባኛልዎን በተቻለ ፍጥነት መጠየቅ፣
- በተቻለ ፍጥነት አገግመው ወደ ሥራ እንዲመለሱ እንዲረዳ የተቀየሱትን እንቅስቃሴዎች በቅልጥፍና መሳተፍ፣
- ወደ ሥራ ለመመለስ የሚቀየሰውን እቅድ ለማዘጋጀት መሳተፍና መተባበር፣
- ማንኛውን ወደ ሥራ የመመለስ እቅድ ግዴታዎችን መስማማት፣
- ወቅታዊ የመሥራት ችሎታውን የሚገልጽ ሰርቲፊኬትና ሌሎች ደጋፊ መረጃዎችን ማቅረብ፣
- በሚችሉ ጊዜ ወደ ተስማሚ ሥራ መመለስ።

## Your employer’s obligations የአሠሪዎ ግዴታዎች

አሠሪዎ የማገገምዎን እና ወደ ሥራ መመለስዎን እንዲደግፍ እንጠብቃለን፡

- የሥራ ላይ ጉዳትዎን ለይገባኛል ወኪላቸው ማስታወቅ ወይም በሥራ ላይ ስለደረሰብዎ ጉዳት ወይም በሥራ ላይ ጉዳት ይገባኛል በ5 የሥራ ቀኖች ውስጥ መጠየቅ፣
- የማገገምዎን እና ወደ ሥራ የመመልስዎን የሥራ እንቅስቃሴዎች መደገፍ፣
- ወደ ሥራ የመለስዎ እቅድ ዝግጅት ላይ መሳተፈና መተባባር፣
- ወደ ሥራ የመመለስዎ እቅድ ላይ በተጠቀሱት ግዴታዎች መስማማት፣
- ከጉዳትዎ በሚያገግሙበት ጊዜ ያለችግር መሥራት የሚችሉትን ተስማሚ ሥራ መስጠት፣
- ጉዳቱ ሳይደርስብዎት በፊት ሲሠሩት ወደ ነበረው ሥራ መመለስ ካልቻሉ፣ ካገገሙ በኋላ ወደ ሥራ ሲመለሱ ተስማሚ ሥራ ላይ ማሰማራት።

## Your support team የእርስዎ የድጋፍ ቡድን

የሚከተሉት ሰዎች ከጉዳትዎ እንዲያገግሙና ወደ ሥራዎና ወደ ህበረተሰቡ እንዲመለሱ ለመርዳት ሊሳተፉ ይችሉ ይሆናል፡

### የጉዳይዎ አስተዳዳሪ

የጉዳይዎ አስተዳዳሪ የመጀመሪያው አገናኝ በመሆን የሚያስፈልግዎትን ድጋፍና አገልግሎቶች በማስተባበር በተቻለ ፍጥነት አገግመው ወደ ሥራዎ እንዲመለሱ ያደርጋል። ለእርስዎና ለአሠሪዎ ፋጣን እና የግል ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ በተቻለ ፍጥነት ከጉዳትዎ አገግመው ወደ ሥራዎ እንዲመለሱ ያስተባብራሉ።

በተጨማሪም፣ እርስዎን እና አሠሪዎን፣ ምንአልባት ከሥራዎ ከአራት ሳምንት በላይ የሚቀሩ ከሆነ፣ ወደ ሥራ የመመለስ እቅድ በመንደፍና ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ ይረዳሉ።



ReturntoWorkSA
Return to *work.*
Return to *life.*

## ዶክተር

ዶክተርዎ ከእርስዎ ጋር በመሆን ጉዳትዎን በመገምገም ምን ዓይነት ሕክምና እንደሚያስፈልግዎት ይወስናል። የህክምና ግብዎን በወወሰን እና በማገገምዎ አዘገጃጀት ላይ እና ወደ ሥራ የመመለስ እቅድ አስተዋጾ እንዲያደርጉ ይረዳሉ።

የተሻለና ተገቢውን ጥሩ ውጤት ለማረጋገጥ፣ በሕክምና እቅድዎ ላይ በቅልጥፍና መሳተፍ በጣም አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ሕክምናዎ እንዴት እየተካሄደ እንደሆነ አስተያየትዎን ለዶክተሩ ቢሰጡ፤ ለእርስዎ ሁኔታ የሚስማማ የህክምና እቅድ እንዲያዘጋጅልዎ ሊረዳ ይችላል።

## ተባባሪ የጤና ሰጪዎች

ዶክተርዎ በግልዎ ጉዳትዎን በመቆጣጠር ወደ ሥራዎ ለመመለስና ሕይወትዎን ለመምራት እንዲችሉ፣ ሕክምና፣ ምክርና ድጋፍ ለሚያደርጉ ለተባባሪ የጤና ሰጪ ድርጅቶት ይመሩዎት ይሆናል።

## ወደ ሥራ የመመለስ አገልግሎት ሰጪዎች

የእርስዎ ጉዳይ አስፈጻሚ ምንአልባት ወደ ሥራ የመመለስ አገልግሎት ሰጪዎች፣ በሥራ ምደባ፣ ሥልጠና ወይም ሌላ ሙያተኞችን ማለትም እንደ አኩፔሽናል ቴራፒስት (occupational therapist)፣ ወይም ፊዚዮቴራፒስት (physiotherapist) በማሳተፍ እንዲዘጋጁና ወደ ሥራ እንዲመለሱ ማድረግ ይችላል።

## ወደ ሥራ የመመለስ አስተባባሪ

አሰሪዎ 30 ወይም ከዚያ በላይ ሠራተኞች ቀጥሮ ከሆነ፣ አገግመው ወደ ሥራዎ ለመመለስ እንዲችሉ ድጋፍ የሚሰጥ የሰለጠነ ወደ ሥራ የመመለስ አስተባባሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። የእርስዎ አስተባባሪ የሚከተሉትን በማድረግ ይረዳል፡

- የይገባኛል ቅጹን እና ሌላ የጽሑፍ ሥራዎችን በመሙላት መርዳት፣
- ከእርስዎና ከጉዳይዎ አስተዳዳሪ ጋር መገናኘት፣
- በሥራዎ ላይ እንዲቆዩ ወይም ወደ ሥራአዎ እንዲመለሱ ማገዝ፣
- ከእርስዎ፣ ከይገባኛል ወኪሉና ከህክምና ሰጪዎቹ ጋር ግንኙነቱን መጠበቅ፣
- እንደገና ጉዳት ደርሶብዎ ወይም እንደገና እንዳይጎዱና እንዳይሰቃዩ የመከላከል እርምጃ መውሰድ፣
- ወደ ሥራ የመለስ እቅድ በማዘጋጀት ማገዝ፣
- ችሎታዎን እና ወደ ሥራ የመመለሱን ሂደት መከታተል፣

የሚሠሩበት ቦታ አስተባባሪ ከሌለው የጉዳይዎን አስተዳዳሪ በምን አይነት ሊረዳዎት እንደሚችል ያነጋግሩ።

## ተጨማሪ መረጃ

ወደ ሥራ መመለስደአን ከእንግሊዝኛ በተለየ ቋንቋ መገኛኘት ከፈለጉ፣ እባክዎን የትርጉምና የማስተርጎም አገልግሎት ማእከልን በ 1800 280 203 ደውለው በ 13 18 55 ደውለው እንዲገናኙን ይጠይቁ። ይህ የማስተርጎም አገልግሎት ምንም አያስከፍልዎትም።



ReturntoWorkSA
Return to *work.*
Return to *life.*